United States Department of Agriculture

# የ USDA የማዳላት ተግባርን ላለመፈጸም የወጣ መግለጫ

የ SNAP እና የ FDPIR የስቴት ወይም በአካባቢው የሚገኙ ኤጀንሲዎች፣ እንዲሁም በስራቸው የሚተዳደሩ ተቋሞች፣ ይህንን የማዳላት ተግባርን ላለመፈጸም የወጣውን መግለጫ መስቀል ይኖርባቸዋል፤

በፌደራልዊ ሕግና በ U.S. Department of Agriculture (USDA) ሲቪላዊ የመብት መመሪያዎችና ፖሊሲዎች መሰረት፣ የ USDA፣ ኤጀንሲዎቹ፣ ቢሮዎቹና ሰራተኞቹ፣ እንዲሁም ገግሞ በ USDA ፕሮግራሞች ላይ የሚሳተፉ ወይም የሚተዳደሩ ተቋሞች በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ የትውልድ አገር፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ስንክልና ምክንያት የማዳላት ተግባር እንዳይፈጽምና፣ በ USDA በሚካሄዱ ወይም ፈንድ በሚደረጉ ያሆኑ ፕሮግራሞች ወይም ተግባሮች ውስጥ፣ ከዚህ በፊት በነበሩ የሲቪላዊ መብት ጥያቄ ተግባሮች ምክንያት የበቀል ወይም የአጸፋ ምላሽ ተግባር እንዳይፈጽሙ ተከልክለዋል።

ስንክልና ያላቸው ሰዎች፣ ይህንን ፕሮግራም አስመልክቶ ሌላ አማራጭ የመግባቢያ መንገድ (ለምሳሌ፣ ብሬል፣ ጎላ ባሉ ፊደሎች የተጻፈ ወረቀት፣ ኦውዲዮቴፕ፣ የሜሪካን አገር የዲዳ የምልክት ቋንቋ፣ ወዘተ) የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ ለጥቅሞች ማመልከቻ ከሞሉበት ኤጀንሲ (የስቴት ወይም ባካባቢው የሚገኝ) ጋራ መገናኘት ይኖርባቸዋል። ዲዳ፣ የማዳመጥ ችግር ያለባቸው ወይም የመናገር ችግር ያለባቸው ሰዎች ከ USDA ጋር በ Federal Relay Service በስልክ ቁጥር (800) 877-8339 በኩል መገናኘት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም፣ ፕሮግራሙን አስመልክቶ የተዘጋጀ መረጃ በሌላ ቋንቋዎችም ተዘጋጅቷል።

የማዳላት ተግባር ተፈጽሞብኛል ብለው የክስ ወረቀት ለማስገባት ከፈለጉ፣ ይህንን በኦንላይን ላይ በ How to File a Complaint ወይም በማንኛውም የ USDA ቢሮ ውስጥ የሚገኘውን የ USDA Program Discrimination Complaint Form፣ AD-3027 ይሙሉ ወይም ደግሞ ወደ USDA ደብዳቤ መጻፍ ይችላሉ። በደብዳቤውም ላይ በፎርሙ ላይ የተጠየቁትን መረጃዎች ሁሉ መጻፍ ይኖርብዎታል። የክስ መመስረቻ ቅጽ ግልባጭ እንዲላክልዎ ለመጠየቅ ወደ **(866) 632-9992** ይደውሉ። የሞሉትን ቅጽ ወይም ደብዳቤ ወደ USDA በሚከተሉት መንገድ ማስገባት ይችላሉ፤

(1) ፖስታ፤ U.S. Department of Agriculture
Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
1400 Independence Avenue, SW
Washington, D.C. 20250-9410፣

(2) ፋክስ፤ (202) 690-7442፣ ወይም

(3) ኢሜይል፤ program.intake@usda.gov.

ይህ ተቋም ለሁሉም ሰው እኩል ዕድል የሚሰጥ ነው።

**ኦክቶበር 14, 2015**